# የላጭን እናት፣ ቅማል በላት!

**ለብሳ የማታውቀውን፣ የሰው ጃኖ ለብሳ፤**
**ተመለሽ ቢሏት ወይት ተመልሳ።**

በቅርብ ወራት ውስጥ በወላይታ ሶዶ አካባቢ የቢቢሲ ጋዜጠኛ ላቀረበው ሐቀኛ ዘገባ የወያኔው ካድሬ ቤን ወይም ቢኒያም በተቃራኒው የሠራውን ድራማ በጹሑፍ መልክ አቅርቤዋለሁ።
ሆኖም ስለ አርዕስቱ ከማተቴ በፊት ስለ ወላይታ አካባቢ የማውቀውን ያህል ትንሽ ለበል።
በ1960ዎቹ ዓ ም በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ ንግሥ የወላይታ አውራጃ ከተማ ሶዶ ሕይወት ያለው አካባቢ ነበር። በዚያን ወቅት ውብ ከነበሩት የድሬ ደዋና ና የናዝሬት ከተማዎች ሶዶ ለየት ያለ ባሕሪ ያለው፤የሰውን ሕይወት ከሌሎች ፍጡራን ጋር ያዛመደ ፤ የተፈጥሮ ልምላሜ የሚታይበት አውራጃ ነበር። በተለይ በዓለም ባንክ ይረዳ የነበረው የዋዱ የእርሻ ልማት ይህን አካባቢ የሕህል ጎተራ ከማስመሰሉም ሌላ ሶዶን ያካባቢው የዳቦ ቅርጫት አድርጓታል።
በዚያን ዘመን ከወላይታ ወሰን ላይ በጎሙጎፋ ክፍለ ሃገር ምዕራብ አባያ አስተምር ስለነበር ሶዶ ከጓደኞቼ ጋር ለቀለብ ሸመት ብቅ ስንል ችግር አልነበረም። ወፍጮ ቤት ሄደን የጤፉን አይነት አማርጠን ወዲያውኑ ተፈጭቶልን ይዘን እንሄዳለን።
በአስተዳደር በኩል ከማንኛውም የኢትዮጵያ አውራጃዎች የወላይታ አውራጃ እውቅና ብቃት ያላቸው አስተዳዳሪዎች አጋጥመውታል። በ50ዎች ዓ ም ውስጥ ከታወቀው የአሜሪካ ዩኒቨርሲቲ የተመረቁትና 1953 ዓ ም መፈቀለ መንግሥት ሙከራ ያደረጉት ግርማሜ ንዋይና ከአሜሪካን ዩኒቨርሲቲ በቤሩት ከሚገኘው የተማሩት ደጃዝማች ወልደሰማየት የወላይታ አውራጃን አስተዳድረዋል። በእነዚህ ዕውቅ ኢትዮጵያውያን የተመሠረተው ከተማ ምን እንደሚመስል መገመት አያስቸግርም። የከተማው ፕላን የባሕል ማዕከሉና መጽሐፍት ቤቱ ከአካባቢው በበቀለ እንጨትና ቀርቀሃ ወብ በሆነ መንገድ የተሠራ ነው።
ከመሪዎቹ የሕዝቡን ንቃተ ሒሊና መገመት ይቻላል።የወላይታ ሕዝብ የፓለቲካ ንቃት ሒሊና ዛሬም ያለፋትም ገዥዎች ጠቀንቅቀው ያውቁታል።

ለምሳሌ ወያኔ ሃገራችንን ሲቆጣጠር በከፋፍለህና አዳክመህ ግዛው ፖሊሲው ሕዝቦች በቋንቋ በዘር እንዲከፋፈሉ ሲያሴር የዚህ አካባቢ ሕዝብ ግን በአንድነቱ ጸንቶ ቆመ። ያም ለወያኔ የእግር እሳት ሆነበት። ከዚያም አልፎ የወያኔዋ የትምህርት ሚንስትር የነበረቸው፣ ገነት ግርማ ከጡት ማሲያዣዋ አውጣታ የሰጠቸውን የመማሪያ ቋንቋ ወጊጅ ብሏት አማርኛን የመማሪያ ቋንቋ እንዲሆን የመረጠ ነው። ለወላይተ ሕዝብ ይህ በአንድ ጊዜ የመጣ የንቃት ሒሊና ብቃት አይደለም። አብሮት የተፈጠረና በሂደት ያዳበረው ነው።

ወያኔም የወላይታ ሕዝብ በአንድነቱ በመጽናቱ በማስራብ ተበቀለው። የቢ.ቢ.ሲ.ው ዜና አጠናቃሪም



ያጋለጠው ይህንኑ ነው። ጋዜጠኛው የወላይታን ሕዝብ ቀርቦ መጠየቁ የወያኔን የውስጥ ጓዳ ከፍቶ የማየት ያህል ነው።

የቢ.ቢ.ሲ.ው ጋዜጠኛ በማያወላዳ መንገድ በረሃብ ሰቆቃ ሚስታቸው የሞቱባችውን አቶ ቶቡኬ አሽኔንና የረሃብ ሳል እየሳሉ የነበሩትን ወይዘሮ ዲዲቄ አሽኔን በቪዲዮ ቀርፆዎ ለዓለም ሕዝብ አቅርቦታል።

የቢ.ቢ.ሲ.ውን ቅንብር ለማስተባበልና የደቡብ ሕዝብ ተወካይ የሆኑትን ፕሮፌሰር በየነ ቢጥሮስን ከሕብረተሰቡ ለማለያየት ቢኒያም የሚባል የወያኔ ካድሬ የሠራውን ድራማ አይቶ ያላዘነ ኢትዮጵያዊ አለ ለማለት ያስቸግራል። ይህን መሰል ዋልጌ የገዛ ወላጆቹን አንገት የሚያስደፋ ነው። ይህ ሰው ለሰው ልጆች ርህራሄ ባላቸው ከዓለም ዙሪያ መጥተው በመከበበር ከሚኖሩባት ቶሮንቶ ካናዳ ይኖር የነበረ ሲሆን ከሕብረተሰቡ ምንም ቁምነገር አልቀሰመም። ሲበዛ አስመሳይ ነው። ‘ኢትዮጵያ ትቅደም’ Ethiofirst የሚል ዌብ ሣይት ከፍቶ መግቢያው ላይ የኔልሰን ማንዴላን ንግግሩች ቀርጾ ታጋይ መሆኑን መግለጫው አድርጎታል። ትክክለኛውን ሥራውን በወላይታ ሕዝብ ላይ የሰራው ማጭበርበር ማንነቱን ግልጽ አድርጎታል። ባንኛው ሕብረተሰብ ውስጥ ይህን ዓይነት ስብዕና ያላቸው ግለሰቦች የተናቁና የተዋረዱ ናቸው ። ከሁሉም በላይ ሕዝቡ እርዳታ እንዳይደርሰው ከማድረጉ ሌላ ያንን ኩሩ ሕዝብ ለማስፈራራትና ቅስም ለመስበር ጥይት የጎረሰውን ክላሰኮቭ ጠብመንጃውን በመኪናው ውስጥ አስቀምጦ፣ ሪቮርቮር ሽጉጡን በኪሱ ሽጉጦ፣ ማይክሮፎንና ኮፒተር ይዞ መጎራደዱ የማነው ቴክስ ? እስከማለት ተደርሷል። ሌላው ደግሞ ለከት የለሽ ውሸቱን ከእኛ አዛውንት አፋ ውስጥ ከቶ እንዲያስተጋቡለት ሲገፋፋቸው በመጸጸት አንገታቸውን ሰበር አደረጉ። ፎቶውን ይመልከቱ።

ሕዝቡም በመገረም አፉን ያዘ።እኝህ አዛውት አያቱ አይሆኑም። እርሳቸውን ማስጨነቅስ ነበረበት? አቶ ቶቡኬ አሼኔና ወይዘሮ ዲዲቄ አሼኔ ከቢቢሲ ጋዜጠኛ ጋር ያደረጉትን ቃለ ምልልስና ከዚህ የወያኔ ልሙጥ ጋዜጠኛ ጋር ያደረጉትን ቃለ ምልልስ ብታጤኑት ይህ ወጣት የቱን ያህል የከንቱ ሕይውት ኖሮ የሌሎችንም ሲያል ለማድረግ እንደሚጥር ያሳያል።አያልቅበት ውሸት የአቶ ቶቡኬ ባለቤት ሐውልት ማሳየቱ ነው።




ከዚያ ቀልጣጣ ሜዳ ላይ ቤተክርስቲያን በሌለበት የመስቀል ቅርጽ ተቀርፆበት ማሳየቱስ?። በዚያ መንገድ በሌለበት ድንጋይ አጓጉዞ የአንድ ከረጢት ሲሚንቶ ዋጋ አራት መቶ ብር ገዝቶ ይህን ሐውልት ማሰራት ይቻላል? አቶ ቶቡኬ አሼኔ በረሃብ ለሞተችው ሚስታቸው ሐውልት ለማሰራት ገንዘቡንስ ከየት አመጡት። አቶ ቶቡኬንና ወይዘሮ ዲዲቄንም ሳልቧጅ ውራጅ አልብሰው ሊያሸሞነሙናቸውም ሞክረዋል። የወላይታ ሕዝብ ይህቺን ዓይነት ይገባዋል። አልሰሜ ‘የላጭን እናት ቅማል በላት’ ነው።






ይህ ሒሊና ቢስ የወያኔ ጋዜጠኛ ከፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ በላይ ስለወላይታ ሕዝብ አውቃለሁ ማለቱ የቱን ያህል የአእምሮ በሽተኛ መሆኑን ያሳያል። የቡርቃው ዝምታና ተራራውን ያንቀጠቀጠው ትውልድ የፃፈውን ተስፋዬ ገብረአብን አስታወሰኝ ። ሕውሃት ሃገር ሲቆጣጠር ጋዜጠኛ ነኝ ብሎ ስለኦሮሞ ሕዝብ ከእኔም በላይ አዋቂ ብሎ ቀርቦ ነበር። አሁን ግን በግልባጩ የወያኔ ጠላት ሆኖ እንደእውቁ ባንከኛ ተፈራ ደገፌ ጺሙን ከርክሞ ያለፈውን የዱብዱብ ሥራውን አውገዞ ሱባዔ ገብቶ እናየዋለን። ቤንም በቅርቡ በመካከላችን እንሚሆን አልጠራጠርም። ይህን ዓይነቶቹ ግለሰቦች ዲን የላቸውም። ያለ ሞያቸው ገብተው ያቦካሉ። ሕዝባችን ለነዚህ ዓይነቶች ስም አለው።




ለብሳ የማታውቀውን፣ የሰው ጃኖ ለብሳ፤ተመለሺ ቢሏት፣ ወዴት ተመልሳ፤ ይልላቸዋል።
ይህ እንዳይሆን፣ ትምህርት እንዲሆን በተረት መልክ የሚነገሩ ብዙ ተረቶች አሉ።በሃገራችን አሁን የሚታየው ሁኔታ ይህቺን ተረት በማስቀመጥ ልሰናበት።
ሁለት ግለሰቦች አንደኛው ከሰሜን ሌለኛው ከደቡብ በተቃራኒው ይጓዛሉ። መሐል ሥፍራ ላይ ይገናኛሉ። ስለጉዟቸው ከተጠያየቁ በኋላ፤ ስለሞያቸውም መጠያየቅ ይጀምራሉ። በቦታው የሚፈሩት ዳኛ አልነበረምና ሁለቱም በሌባነት ራሳቸውን ያስተዋውቃሉ። አንደኛው ደፈር ብሎ ‘በእውነት ሌባ ከሆንክ ያቺ በዛፉ ላይ ዕንቁላሎቿን ታቅፉ የተቀመጠችው አሞራ ሳትቀሳቀስ ዕቁላሎቿን ስረቅ’ ይለዋል። ዕቁላሉን ለመስረቅ ከዛፉ ይወጣል። ጠያቂውም ተከትሎት ይወጣል። የመጀመሪያው ከአሞራዋ ሥር እየሰረቀ ከኪሱ ሲከት ያኛው ደግሞ ከእርሱ ኪስ እየሰረቀ ከራሱ ኪስ ይከታል። ቀድሞት ይወርድና ‘የታለ የሰረከው ዕቁላል’ ይለዋል። ኪሱን ሲዳብስ ዕንቁላሉ የለም። ሁለተኛው ሌባ ከኪሱ እንደሰረቀው ያሳየዋል። ሁለቱም እርስ በርስ ታማኝ ሌቦች ሆነው በጋራ ሃገር አወደሙ።

ሃገራችን ኢትዮጵያ ዛሬ የገጠሟት ታማኝ ሌቦች ለወገን ደንታ የሌላቸው ለራሳቸው የሚኖሩ ተዋርደው ሃገር የሚያዋርዱ ናቸው።

እግዚያብሔር ኢትዮጵያን ከሚሰርቋት ልጆቿ ያድናት።

ታደለ መከሪያ
tadele@shaw.ca